# *ምንድነዉ ግርግር?*

ከንጉሤ ጋማ

የእስራት፡ የፍርሃት፣ሃዘን ባጠላበት የሰቆቃ ምድር
ክህደትና ስርቆት፣ዉሸት በበዛበት፣ ለቃል ሳይታደር
ባዶ ከንቱ ጩኸት፣ድምፅ ሳይከበር፣ ምንድነዉ ግርግር?

በሩጫዉ ሜዳ ላይ፣ ያለ ተቀናቃኝ፣ ከዚህ ከዚያ መለስ
ብቻህን ሩጠህ፣ ብቻህን ልትጨርስ፣ ለዉጤት ለመድረስ፡
ሳይጀመር ታዉቋል፣ ተጠናቋል አሉ ፣ ዝግጅትህ ሁሉ
ዳሩ ምን ሊያግድህ ፣ አግዓዚ፡ ፌዴራል፣ ከደገፊህ ኃይሉ፡፡

የመንበርህ ግብር፣ የንግስናህ ቅባት
የሕፃን ያዛዉንት ደም የሚፈስበት፣
ካራ መከትከቻህ፣ ቢላዋህ ተሳለ?
ለዕርድ፣ለድግስህ፣ ዳስ ድንኳን ተጣለ?

ለሆዱ ያደረ፣ አብሮህ እበላ ባይ፣ እስካለ ከጎንህ
ያፈሰስከዉን ደም፣ ተረማምዶ ረግጦ፣ የዛሬን ካጀበህ፣
አለቀ፡ ደቀቀ፣ ምን ትፈልጋለህ?
አርቀህ ካላየህ፣ ኋሊና ከሌለህ
በቃህ ከዚህ ወዲያ፣ ምን ትጠብቃለህ?

አንተም ሆንክ እነሱ፣ በዙሪያህ የቆሙት ግና ልብ በሉት
ከታሪክ ከትዉልድ፣ ፍርድና ዳኝነት፣ እንደማታመልጡ እዉነቱን ተረዱት፡፡

ዛሬማ! ሥልጣንና ጥቅም፣ እንሰሳ አድርገዋችሁ፣ ነገ አይታያችሁ
ጊዜን ጊዜ ሽሮት፣ በሠፈሩት ቁና መሠፈር እንዳለ፣ አይታሰባችሁ፡፡